የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፶፪
አዲስ አበባ መጋቢት ፲፮ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

22nd Year No.52
ADDIS ABABA 25th March, 2016

ደንብ ቁጥር ፫፻፹፩/፪ሺ፰ ዓ.ም

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት (ማሻሻያ) ደንብ ......................ገጽ ፰ሺ፱፻፴፯

Regulation No.381/2016

Ethiopian Electric Power Establishment Council of Ministers (amendment) Regulation ..........................................Page 8937

### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፹፩ /፪ሺ፰

### የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብን ለማሻሻል የወጣ ደንብ

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፪/፪ሺ፭ን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፮/፪ሺ፰ አንቀጽ ፭ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ፳፩እና ፵፯(፩)(ሀ) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት (ማሻሻያ) ደንብ ቁጥር ፫፻፹፩/፪ሺ፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. ማሻሻያ**

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፪/፪ሺ፭ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፦

፩/ የደንቡ አንቀጽ ፭ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፭ ተተክቷል፤

"፭. ዓላማ

ድርጅቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፦

### Council of Ministers Regulation No. 381 /2016

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO AMEND THE ETHIOPIAN ELECTRIC POWER ESTABLISHMENT REGULATION

WHEREAS it has become necessary to amend the Ethiopian Electric Power Establishment Council of Ministers Regulation No. 302/2013;

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 916 /2015 and Article 21 and 47(1) (a) of the Public Enterprise Proclamation No. 25/1992.

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as the "Ethiopian Electric Power Establishment Council of Ministers (amendment) Regulation No381/2016".

**2. Amendment**

The Ethiopian Electric Power Establishment Council of Ministers Regulation No. 302/2013 is here by amended as follows:

1/ Article 5 of the Regulation is deleted and replaced by the following new Article 5:

"5. Purposes

The purposes for which the Enterprise is established are:

፩/ ከብሔራዊ ግሪድ ጋር የተያያዙ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫዎች፣ ከ ፷፮ ኪሎቮልት በላይ የሆኑ ማስተላለፊያ መስመሮችና ማከፋፈያ ጣቢያዎች የግንባታ ሥራዎች የአዋጭነት ጥናት፣ የንድፍ እና የቅየሳ ሥራዎች ማከናወን፣ እንደአስፈላጊነቱ እነዚህኑ ሥራዎች በኮንሰልታንት ማሠራት፤

፪/ ከብሔራዊ ግሪድ ጋር የተያያዙ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫዎች፣ ከ ፷፮ ኪሎ ቮልት በላይ የሆኑ ማስተላለፊያ መስመሮች እና ማከፋፈያ ጣቢያዎች የግንባታና የማሻሻያ ሥራዎችን ማከናወን ፤እንደአስፈላጊነቱ እነዚህኑ ሥራዎች በሥራ ተቋራጭ ማሠራት፤

፫/ ከብሔራዊ ግሪድ ጋር የተያያዙ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጪያ ጣቢያዎችን፣ ከ ፷፮ ኪሎ ቮልት ኃይል በላይ የመሸከም አቅም ያላቸውን የኤሌክትሪክ ማስተላለፊያ መስመሮችን እና ማከፋፈያ ጣቢያዎችን ማስተዳደር፣ የኦፕሬሽን እና የጥገና ሥራዎችን ማከናወን፤

፬/ ከ ፷፮ ኪሎ ቮልት ደረጃ በላይ በሆኑ መስመሮች የኤሌክትሪክ ኃይልን በጅምላ መሸጥ እና መግዛት፤

፭/ ከ ፷፮ ኪሎ ቮልት በላይ የሆኑ የኃይል ማስተላለፊያ መስመሮችን ሊዝ ማድረግ፤

፮/ የሚሸጠውን የኤሌክትሪክ ኃይል በተመለከተ የታሪፍ ማሻሻያ ሀሳብ ማቅረብ፣ሲፈቀድም ተግባራዊ ማድረግ፤

፯/ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የሚያወጣውን መመሪያና የፖሊሲ አቅጣጫ መሠረት በማድረግ ቦንድ መሸጥና በዋስትና ማስያዝ እና ከአገር ውስጥ፣ ከውጭ የገንዘብ ምንጮች ጋር የብድር ውል መደራደርና መፈራረም፤

፰/ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ የሆኑ ሥራዎችን ማካሄድ።"

፪/ የደንቡ አንቀጽ ፮ ተሽሮ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፮ ተተክቷል፤

1/ to undertake feasibility studies, design and survey of electricity generation in integrated national grid, construction of transmission lines and substation over 66 kilo volt level; to contract out such activities to consultants, as required;

2/ to undertake construction and up grading of electricity generation in integrated national grid and, construction and up grading transmission lines and substation of over 66 kilo volt level; to contract out such works to contractors as required;

3/ to administer, operate and maintain electricity generation in the integrated national grid, and transmission lines and substation of over 66 kilo volt level;

4/ to sell and purchase bulk electric power on transmission lines above 66 kilo volt level;

5/ to lease transmission lines above 66 kilo volt level;

6/ to submit electricity tariff proposals with respect to power it sales and implement same upon approval;

7/ in line with directives and policy guidelines issued by the Ministry of Finance and Economic Cooperation to sell and pledge bonds and to negotiate and sing loan agreements with local and international financial sources;

8/ to undertake any other related activities necessary for the attainment of its purposes."

2/ Article 6 of the Regulation is repealed and replaced by the following new Article 6;

"፮. ካፒታል

ለድርጅቱ የተፈቀደው ካፒታል ብር ፩፻፳ ቢሊዮን (አንድ መቶ ሃያ ቢሊዮን ብር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፴ ቢሊዮን (ሰላሣ ቢሊዮን ብር) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል።"

፫. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ መጋቢት16 ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም.

ኃይለማርያም ደሣለኝ
የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

"6. Capital

The authorized capital of the Enterprise is Birr 120,000,000,000 (One Hundred Twenty Billion) of which 30,000,000,000 (Thirty Billion) is paid up in cash and kind."

3. Effective Date

This Regulation shall come into force on the date of its publication on the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 25th day of March, 2016**

**HAILEMARIAM DESSALEGN**
**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት